MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት

8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
Tel: (202)-677-0094 Fax:
Web: http//www.moreshwegenie.org/



# ሞረሽ የዐማራ ድምፅ የሬድዮ ጣቢያ ማቋቋም ለምን አስፈለገ?

ባለፉት ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት በዐማራው ላይ የሚፈጸመው የዘር ማጥፋት እና የዘር ማጽዳት ዘመቻ ከችግሩ ሥፋት እና ጥልቀት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ የሚዲያ ሽፋን አልተሰጠውም። በ«ኢትዮጵያዊነት» ስም በተቋቋሙት ድርጅቶችም ሆነ በተለያዩ አገሮች መንግሥታት ሥር የሬድዮ እና የቴሌቪዥን መርኃ-ግብሮችን በአማርኛ ቋንቋ የሚያሠራጩ ሚዲያዎች በዐማራው ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እና በደል የዓለም ማኅበረሰብ እንዲያውቀው የማድረግ ፈቃደኝነታቸው እጅግ ውስን መሆኑን በተደጋጋሚ ታይቷል። ይህም «ችግሩ ችግራችን ነው» ብሎ የሚይዝ ሚዲያ አለመኖሩን ያረጋግጣል። ስለሆነም እኛ የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አባሎች እና ደጋፊዎች ለመላው የዐማራ ሕዝብ ድምጽ የሚሆን የሬድዮ ጣቢያ ለማቋቋም ቆርጠን ተነስተናል። ዐማራው በተገንጣይ እና ጠባብ የጎጠኞች ቡድኖች የተከፈተበትን የሥነ-ልቦና ጦርነት ተመጣጣኝ በሆነ ኃይል በመመከት እውነተኛውን ገፅታ ለማሣየት፣ የሚያስችል የአጸፋ ፕሮፓጋንዳ እና ቅስቀሣ ለመሥራት፣ **«ሞረሽ የዐማራ ድምፅ ሬድዮ»** በአየር ላይ መዋል ለነገዳችን ህልውና በጣም አስፈልጓል።

ለሩብ ምዕተ-ዓመት በዘለቀው የትግሬ ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ፣ ከ፭(አምሥት) ሚሊዮን በላይ ዐማሮችን በልዩ ልዩ መንገዶች ከምድረ ገፅ እንዲጠፉ ተደርጓል። ይህን ወንጀል የፈፀሙ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን ለፍትኅ ለማቅረብ የተቀነባበረ የመረጃ ልውውጥ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። የዐማራውን ነገድ ለመታደግ የሚቻለው ዐማራው ተደራጅቶ በኅብረት ጥቃቱን ሲመክት ነው። ሰለሆነም ዐማራው የሚፈጸምበትን የዘር ማጥፋት እና የዘር ማጽዳት ወንጀል ለመቋቋም የሚችለው፣ በጠንካራ መሠረት ላይ ተደራጅቶ የሚደርስበትን ጥቃት ለመቋቋም ሲዘጋጅ መሆኑን መቀመበል ያስፈልጋል። ለዚህም ተጣጣኝ የሥነ-ልቦና ትጥቅ ለመታጠቅ የሬድዮ ድምጽ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ የዐማራው ልጆች «የወገናችን ችግር ችግራችን ነው፤ ብሦቱም ብሦታችን ነው፤ ከሁሉም በላይ ዘራችን መጥፋት የለበትም» ብለን ከተነሣን፣ እንኳንስ እንዲት የአጭር ሞገድ የሬድዮ ጣቢያ ማቋቋም ቀርቶ፣ ሁሉን-አቀፍ የሆነ የዐማራ ሚዲያ ማዕከል ለመመሥረት መቻላችን ጥርጥር የለውም።

በመሠረቱ የዐማራው ሕዝብ ጠላቶች በቅድሚያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው። ዐማራው እንዲጠፋ የተወሰነበት አብይ ምክንያት በታሪኩ የሚተማመን፤ አትንኩኝ ባይ፤ ለነፃነቱ ቀናዒ፤ ለህልውናው እና ለአገር ዳር ደንበር ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር ሟች ፍፁም ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ነው። በዐማራው ነገድ ላይ ጥቃት የተጀመረው ዛሬ ሣይሆን ከ፭፻(አምሥት መቶ) ዓመታት በፊት በቱርኮች እና በአረቦች ድጋፍ ግራኝ አሕመድ ካካሄደብን የጅምላ ጭፍጨፋ ጀምሮ እንደሆነ ይታወቃል። ከግራኝ ጭፍጨፋ ተከትሎ የኦሮሞዎች ወረራ ተከተለ፤ ከዚያም በዘመነ-መሣፍንት ከፍተኛ የሆነ ዕልቂት የደረሰው በዐማራው ላይ ነበር። ፋሽስት ኢጣሊያም ከአንዴም ሁለቴ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሰችው በዐማራው ላይ ነበር። ደርግ ገና ሥልጣን ከመያዙ አስቀድሞ የዘመተው በዐማራው ላይ መሆኑ የቅርብ ዘመን ትውስታችን ነው። የትግሬ-ወያኔ ዘረኞች ገና ከጠዋቱ በርሃ ሲገቡ ጀምረው በፕሮግራማቸው ያሰፈሩት ዋና ጠላታቸው ዐማራ እንደሆነ እና ከተቻለም ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ እንዲጠፋ፣ ካልሆነ ደግሞ አቅመቢስ ባርያቸው አድርገው ለመግዛት መሆኑ ግልፅ ነው። ይህንን ጽኑ ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ ከበረሃ ጀምረው በዐማራ ሕዝብ ላይ በፍርሃት ተጨምድደው በመሠረቱት ጥላቻ፣ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስሙን ጥላሸት ቀብተውታል፤ መሬቱን ቀምተውታል፤ በአገሩ ላይ ሁለተኛ ዜጋ በማድረግ ከኖረበት ቀዬው እንዲፈናቀል አድርገውት እናያለን። ለዚህም ማረጋገጫው ላለፉት ፶(ሃምሣ) ዓመታት በሻቢያ፣ በትግሬ-ወያኔ እና በኦነግ አማካይነት በዐማራው ሕዝብ የተፈጸመው የሥነ-ልቦና ጥቃት ሕዝባችንን ከነበረበት በራስ የመተማመን ደረጃ አወርዶት ይገኛል። ዐማራው ይህን በረቀቀ እና በግልፅ በተቀነባበረ ሥልት የሚፈፀምበትን አደገኛ የሥነ-ልቦና ምት፣ ሁለገብ የዘር ማጽዳት እና የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሊቋቋም የሚችለው በአንድ ዐላማ ሥር አንድ ሆኖ ሲቆም ብቻ ነው። ስለሆነም «ሞረሽ የዐማራ ሬድዮ ድምፅ» የተጎዳውን የወገኖቻችን ሥነ-ልቦና ለማደስም ሆነ የወንድማማችነት መንፈስ ለማጎልበት ያገለግለናል።

ለአንድ ዓላማ ግብ መምታት በሥርዐት ላይ የተመሠረተ ዝግጅት እና መሠናዶ እጅግ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ይህ አካሄድ በግል ሕይዎታችንም ስኬት ለማግኘት ያስችላል። ለመዘጋጀት እና ለመስናዳት ደግሞ ቅንብር እና ድርጅት ያስፈልጋሉ። መደራጀት ጠላትን ለይቶ ለመመከት እና አሸንፎ ለመውጣት ያግዛል።

*መደራጀት ተመጣጣኝ ኃይል ፈጥሮ በማናቸውም ጊዜ እና ቦታ  ለድርድር ያበቃል። ስለሆነም የሬድዮው ድምጽ በትግሬ-ወያኔ የተመዘዘበትን የጥፋት ሰይፍ ወደ አፎቱ ለማስገባት ዐማራው ለአንድ ዓላማ፣ በአንድ ልብ፣ በፍጹም የወንድማማችነት መንፈስ መነሣት እንዲችል፣ በእውነት እና በእውቀት ላይ የቆመ የፕሮፓጋንዳ እና የቅስቀሣ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ፍቱን መሳሪያ ነው። ሞረሽ የዐማራ ድምጽ ሬድዮ «ዐማራው ከገባበት አጣብቂኝ ወጥመድ ሰብሮ ለማምለጥ ምን ማድረ አለበት? እንዴትስ በይፋ በአገር አቀፍ ከታወጀበት የዘር ማጽዳት ሤራ እርምጃ ሊተርፍ ይችላል?» የሚሉትን እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በመዳሰስ በኢትዮጵያ ምድር እንደስፌድ ቆሎ ተብትኖ ለሚገኙት ዐማራ ወገኖቻችን ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን እንዲደርስ ያደርጋል።*

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የካቲት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. በቁጥር ሞወዐድ 000100-08 «ሞረሽ የዐማራ ድምፅ ሬድዮ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የእርዳታ ማሰባሰቢያ ጥሪ» በዓለም ለሚገኙ ዐማራ ወገኖች እና ወዳጆች ማቅረቡን በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ እንወዳለን። «ለወገን ችግር ፈጥኖ ደራሹ ወገን ነውና» በሜልበርን (አውስትራሊያ) እና በካልገሪ (ካናዳ) የሚገኙ የሞረሽ-ወገኔ መሠረታዊ ማኅበራት አባሎች እና ደጋፊዎች የጉዳዩን አጣዳፊነት እና አስፈላጊነት ጠንቅቀው በመገንዘባቸው፣ እሑድ የካቲት 27 ቀን 2008 ዓ.ም. የመጀመሪያ ዙር የገንዘብ እርዳታ ማሰብሰብ ዝግጅት አከናውነዋል። ይህ ጥረት በሚገባ ተጠናክሮ በሁሉም የዓለማችን ክፍሎች ሊቀጥል ይገባዋል። ዐማራው ከገባበት የሚያባራ ጥቃት እና ሰለባ ሊያመልጥ የሚችለው፣ በንጹህ የመላው ዐማራ የወንድማማችነት/እህትማማችነት መንፈስ በአንድነት ቆሞ በምድር ውስጥ የቁም ስቃይ እና መከራ ለሚበላው ወገናችን ድምፅ ሲሆን ብቻ ነው። በመሆኑም «ሞረሽ የዐማራ ድምጽ ሬድዮን» ተረባርበን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለአየር እንድናበቃው በዐማራነታችን የሚጠበቅብንን ግዴታ እንድንወጣ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ጥሪውን ለመላው የዐማራ ሕዝብ ያስተጋባል።*

*የዐማራው ኀልውና ጉዳይ ለዐማራው ብቻ ሊተው አይገባም። የእንቁጣጣሽ በግ ሲታረድ የመስቀሉ በግ ይስቃል እንዳይሆን፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከአገራችን ምድረ ገጽ እንዲጠፋ ከተበየነበት የዐማራ ሕዝብ ጎን በመቆም የዜግነት እና የንፁህ ኢትዮጵያዊ ወንድማማችነት/እህትማማችነት ድርሻ ሊወጣ ይገባዋልና ሞረሽ የዐማራ ሬድዮ ድምጽ እንድትረዱ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናቀርባለን።*

***በግፈኛ ዘረኞች ድምፁ ለታፈነው ዐማራ ድምፅ እንሁነው!***

***ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደጋለን!***

***ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!***

***ኢትዮጵያ በጀግኖች እና ቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም ፀንታ ትኖራለች!***